# ይቅርታ የማይደረግለት አገዛዝ !

ኢህአዴግ ከምርጫ 1997 የተማርኩት ብዙ ነገር አለ አለን። በምርጫ 1997 ዓ.ም ኢህአዴግ በፍጹም ያልጠበቀውን ውርደት በምርጫ ሳጥን ተከናነበው። በግንቦቱ የ1977 ዓ.ም ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በእርግጥም በአገዛዙ ላይ ያለውን ጥላቻ ያረጋገጠበት ቀን ነበር። እስኪዚያ ድረስ አገዛዙ በከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ የህዝቡን አስተሳሰብ ለመበታተን ፣ ኢትዮጵያውነቱን እንዲጠላና በየብሄረ-ሰቡ ጉያ ስር ተሸጉጦ ብሄራዊ ባህርይ ያለው ስራ እንዳይሰራ ያላደረገው ጥረት ይህ ነው አይባልም። ሁሉም በየራሱ ቋንቋ መማርና መነጋገር አለበት በሚለው ፈሊጥ የአንድን የብሄራዊ ቋንቋ መዳበርና ለዕድገት አስፈላጊነት በመርገጥ በአገራችን ሰፋ ያለ ህብረተሰቡን የሚያስተሳስር ባህል እንዳይበለጽግ ያልሞከረው ነገር አልነበረም። በቆራጥ ትግል ይህ ርኩስ ህልሙ ከሸፈበት። ሃይማኖትን ከሃይማኖት በማጋጨት ፣ አንዱን ብሄረ-ሰብ በሌላው ላይ እንዲነሳ በማድረግና የርስ በርስ ዕልቂት በመፍጠር የአገዛዙን ዘመን ለማራዘም የሚችል መስሎት ነበር። ብልሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን አንዳንድ ከጉያው የፈለቁ አድርባዮች የሚሰነዝሩበትን ተንኮልና ጥቃት በመቋቋምና ከመጤፍ ሳይቆጥር ለአገሩ ያለውን ፍቅር በግንቦቱ ሰምንት ምርጫ አረጋገጠለት። አልተማረም የሚባለው ህዝባችን እንደዚያ በብዛት በመውጣት አንድ አገርና ህዝብ በተንኮል መገዛት እንደሌለበት በሰጠው ድምጽ አረጋገጠለት። የምፈልገው ክፍፍልን ሳይሆን ስምምነትንና ሰላምን ፣ ድህነትን ሳይሆን ብልጽግናን ፣ ብሄራዊ ውርደትን ሳይሆን ብሄራዊ ነጻነትን ነው የምሻው ብሎ የቅጩን ነገረው። አንድ አገር ታሪክ የሚሰራበት እንጂ የማንም መፈንጫ እንዳልሆነና በመከፋፈል ሳይሆን በመተባበርና በመደጋገፍ ብቻ አንድ የተከበረ አገር መገንባት እንደሚቻል የኢህአዴግን የአስር አራት ዓመት የተወናበደና የተረበሸ ፖለቲካ ርግፍ አርጎ ጣለው። ወያኔ ግን አሻፈረኝ አለ። እኔ በጠብመንጃ የተቀዳጀኋትን ስልጣን በምንም ዐይነት በሰላም ከምርጫ ሳጥን በወጣ የድምጽ ፍላጎት አልሰጥም አለ። በሰኔው ግልጽ ጭፍጨፋ ማንነቱን አረጋገጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኃይሉንና ስልቱን የባሰ በማጠናከር ፣ የህዝቡን ነጻነት በማፈንና ነጻ አስተሳሰብ እንዳይዳብር የፕሬስ ነጻነት እንዳይኖር በተለያዩ መሰናክሎች በማደናቀደፍ አጠቃላይ የሆነ አምባገነናዊ አገዛዝ አሰፈነ። የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚና ተገዥ በማድረግ አምባገነናዊ አገዛዝን ብቻ ሳይሆን የህዝቡ ሞራል በከፍተኛ ደረጃ እንዲሰበርና ለማኝ እንዲሆን አጠቃላይ ድህነትን አስፋፋ። ድህነት ሲስፋፋ አንድ ህዝብ ሞራሉ ይሰበራል። ሲራብ ሲጠማ አገሩን መዘንጋት ይጀምራል። መውጣት የሚችለውም አገሩን እየጣለ ይሄዳል። በዚህ መልክና በምዕራቦች በተደገፈና በተሠጠ ስልጠና በአለፈው አምስት ዓመት ህዝቡን ረግጦ ሊገዛ የሚችልበት ሰፊ የጭቆና መዋቅር መዘርጋት ቻለ።

አገዛዙ በ2002 ዓ.ም ምርጫ የፈለገው ነገር ቢሆን ላለመሸነፍ ቆርጦ የተነሳበት ጊዜ ነበር። አቶ መለስ ከምርጫ 1997 የተማርነው ትምህርት አለ ሲሉ ይህንን ነበር ያረጋገጡሉን። የተሻለ ዲሞክራት ከመሆን ይልቅ ጨቋኝ ፣ ብልጽግናን አምጪ ከመሆን ይልቅ ድህነትን ፈልፋይ ፣ ብሄራዊ ነጻነትን አስከባሪ ከመሆን ይልቅ ከውጭ ኃይሎች ጋር በሺህ ድሮች በመተሳሰርና መሬታችንን በመሸጥ ውርደትን ለማከናነብ ቆርጦ የተነሱ መሆናቸውን ነው። ከምርጫ 2002 ከአገዛዙና ከተከታዮቹ ስሌት ውጭ የጠበቁ ካሉ የዋሆች ብቻ ናቸው። የአገዛዙን ባህርይና ክንውን ብቻ ሳይሆን የውጭ ኃይሎችም ፣ በተለይም የምዕራቡ ዓለም በጥቁር ህዝብ ላይ ያለውን ንቀትና አመለካከት እንዲሁም የፖለቲካ አሻጥር ያልተገነዘቡ ብቻ ናቸው። ለኛ ለአገር ወዳጆች ግን ከምርጫ 2002 ተቃዋሚው ኃይል ምንም ነገር እንደማያገኝ ግልጽ ነበር። ከኔም ሆነ ከአንዳንድ እህቶችና ወንድሞች የተደረሰበት ግንዛቤ  ተቃዋሚው ኃይል ያሸንፋል ወይም ብዙ ድምጽ በማግኘት በፓርላሜንት ውስጥ የተቃዋሚ ፖለቲካ ያራምዳል የሚል ግምት ሳይሆን የህዝቡን ስሜት በመቀስቀስ የአገዛዙን ዕድሜ ለማሳጠር አንድ ዕድል ሊገኝ ይችል ይሆናል የሚል ግንዛቤ ነበር። የህዝቡ ስሜት እየጋለ በመሄድና ውስጠ-ኃይሉ ሲጠነክር ያ ግዙፍ የሚመስለው ኃይል በህዝብ ቁጣና አመጽ ብትንትኑ ሊወጣ ይችላል የሚል ነበር። እዚህ ላይ እንዲያው አመጽን ለመጋበዝም ሆነ ለመደገፍ አይደለም። በመሰረቱ አንድ ህዝብ ተፈጥሮአዊ ነጻነቱ ሲገፈፍበት ፣ መሬቱ ሲሸጠብትና አካባቢው ሲወድምበት ፣ እንዲሁም ደግሞ ከኢኮኖሚ ዕድገት ይልቅ ድህነትን በየጊዜው ሲከናነብና ሞራሉ ሲከሰከስ ሌላ አማራጭ የሌለው መሆኑን ለማሳየት ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ ምርጫ 2002 ከምርጫ 1997 በብዙ እጅ የሚለይበት ነገር አለ። በዕውቀት ሳይሆን „በድርጅታዊ“ ጥንካሬ አገዛዙ በብዙ እጅ ልቆ የሚገኝ ነበር። ፓርቲውን „ህዝባዊና“ „አገራዊ“ ለማስመሰል  ብዙ አድርባዮችንና ከድህነት ልናመልጥ እንችላለን ያሉትን ወጣቶች በአባልነት በማግበስበስ „ድልን ለመቀዳጀት“ ቆርጦ የተነሳበት ምርጫ ነው። በዚህ ላይ የምርጫ ኮሚሽን ቦርድ በራሱ በአገዛዙ የተደራጀና

የገዢው ፓርቲ አባል የሆኑ የሚመሩት ፣ ፍርድ ቤቱ ፖለቲካዊ ቁጥጥር ያለበትና ለተቃዋሚው ኃይል ምንም መፈናፈኛ እንዳይሰጥ ሆኖ በተዘጋጀ ሁኔታ ውስጥ ነው ምርጫው የተካሄደው። ከዚህ በተረፈ አገዛዝና መንግስት አንድ ላይ የተጨፈለቁበት ፣ የሚቀናቀነውን ኃይል ለመደምሰስ ቆርጦ የተዘጋጀና ተቃዋሚው ኃይል ሊቋቋመው በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ነው እንደዚህ ዐይነት የቀልድ ምርጫ ሊካሄድ የቻለው። የምርጫው ዝግጅትና ሂደት አንድ በተለያዩ የጦር መሳሪያዎች በታጠቀና ጠላቴ ነው የሚለውን ኃይል ሁሉ ለመደምሰሰ ቆርጦ በተነሳና ምንም መሳሪያ በሌለውና በህዝብ ድምጽ ብቻ በመተማመን ለምርጫ በተሰለፈ ኃይል መሀከል ነው የተካሄደው። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በዚህ ዐይነት ተመጣጣኝነት በሌለበት ሁኔታና ሁሉም ነገር ግልጽ በሆነበት አገር ውስጥ ተቃዋሚው ኃይል እንዴት ለምርጫ እወዳደራለሁ ብሎ ሽር ጉድ ለማለት በቃ? የተቃዋሚው ኃይል በዚህ ድርጊቱ  አገዛዙ የፖለቲካ ተቀባይነት(Legitimacy) እንዲኖረው አላደረገም ወይ? ዲሞክራሲ እንዳለ አላስመሰለም ወይ ? ወይስ በእርግጥም የአገዛዙንና የዓለም ማህበረሰብ የሚባለውን አስተሳሰብ በዚህ ዐይነቱ ምርጫ ለመግግታትና ወደ አንዳች ዐይነት ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ሊያመራ የሚችል ሁኔታ መፍጠር ይቻላል ብሎ ተማምኖ ነበር ወይ ? በእርግጥ የተቃዋሚው ኃይል ጭንቅላት ውስጥ ገብቶ እንደዚህ ነበር የሚያስቡት ብሎ አጥጋቢ ትንተና መስጠት ባይቻልም አሁንም እንደትላንትናው የተቃዋሚው ኃይል የማይማረው አንድ ነገር አለ። አሰራ-ዘጠኝ ዐመት ህብረ-ብሄራዊና ማህበረሰብአዊ ባህርይ አገዛዝ ማዳበር ካልቻለ አገዛዝና የባሰውኑ በውጭ ኃይሎች ጉያ ስር እየታሸ ህዝባችንና አገራችንን ከሚያሽ አገዛዝ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝን ማስፈን ይቻላል ብሎ ማመኑ ነው። ከማንኛውም የፖለቲካ ሎጂክና ስሌት የወጣ አስተሳሰብ በተቃዋሚው ጭንቅላት ውስጥ እንደተቀረጸ የአስራ-ዘጠኙን ዓመት የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንቅስቃሴና የፓርቲዎችን ተሳትፎና ትንተና ላነበበ በቀላሉ ሊረዳው ይችላል። ይህ ዐይነቱ የዋህ የፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም ደግሞ ከተወሰነ የፖለቲካ ፍልስፍና የመነጨ የፖለቲካ ግምገማና ተጨባጭ ሁኔታውን ለራስ በሚስማማ መልክ ማንበብ ተቃዋሚው ኃይል እየደጋገመ የፖለቲካ ስህተት እንዲሰራ አስገድዶታል።

## አቶ መለስና ግብረ-አበሮቻቸው የማይማሩት ነገር !

አብዛኛዎች የሶስተኛው ዓለም አገር የፖለቲካ መሪዎች ታሪክ መስራት ማለት ምን ማለት ነው ? አንድ ህብረተሰብስ እንዴት ነው በጸና መሰረት ላይ ሊገነባ የሚችለው ? እንዴትስ አንድ ህብረተሰብ ብዙ ውዝግብ ውስጥ ሳይገባ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ሊሸጋገር ይችላል? የሚለውን መሰረተ ሃሳብ ከመጀመሪያውኑ ጭንቅላታቸው ውስጥ ስለማይቀርጹ ስልጣን  ላይ በሚወጡበት ጊዜ በጠባብ አስተሳሰብ በመወጠርና በውጭ ኃይሎች በመሳሳት ህብረተሰቡን ወደማይሆን አቅጣጫ ይመሩታል። የህዝብን ሀብት የጥቂት በስልጣን ላይ የተቆናጠጡ ባለስልጣኖች ግላዊ ሀብት አድርጎ በመቁጠር ሰፊው ህዝብ ከማንኛውም የሀብት ይዞታና ማፍራት እንዲገለል ይደረጋል። ዛሬ በአፍሪቃና በአገራችንም የሚታየው የስልጣን መባለግ „የገዢ መደቦች“ የህዝብን ሀብት የግላቸው በማድረግና ከውጭ ኃይሎች ጋር በመተሳሰርና በመዝረፍ ድህነትን ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የተዘበራረቀ ሁኔታንና የአካባቢን ቀውስ እንደሚፈጥሩ በዐይናቸን የምናየው ነው። በአፄ ኃይለስላሴ ጊዜ የተፈጸመው ትልቁ የታሪክ ወንጀል ከላይ የሰፈነውን መሰረተ-ሃሳብ በጭንቅላት ውስጥ ካለመቅረጽ የተነሳ ነው። አፄ ኃይለስላሴና አገዛዛቸው የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ህዝብ ባለመቁጠራቸውና ታሪክን መስራት ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት ባለመቻላቸው ህዝባችንን ለአደጋ አጋልጠው አለፉ። ድርጊታቸው ግን ሆን ብሎ የተካሄደ አልነበረም። ከአርቆ አለማሰብና የነገሮችን ውስብስነት በቅጡ ካለመረዳት የመነጨ ድርጊት ነው። የደርግም ፖለቲካ ሆን ብሎና ተሰልቶ አገርን ለማጥፋት የተካሄደ ፖለቲካ አልነበረም። በአቶ መለስ ብልሁና አዋቂው መሪ አስራ-ዘጠኝ ዐመት ያህል ሲካሄድ የነበረው ፖለቲካ ግን በስሌት ላይ የተመሰረተ ፣ ቂም በቀልንና መከፋፈልን እንደ ፖለቲካ ዘይቤ ተወስዶ ህብረተሰቡን ያወካበ ፣ የህዝባችንን ሞራል በዚህም በዚያም ብሎ ለመስበርና ለዝንተ-ዓለም የተልፈሰፈሰና ለውጭ ኃይሎች ተገዢ የሆነ ትውልድ በማፍራት ታሪክ እንዳይሰራ የሚያደርግ ነው። በተለይም ከምርጫ 1997 ዓ.ም በፊት የወያኔን አገዛዝ አዝማሚያ ደስ ያላላቸውና አደገኛነቱን የተገነዘቡ ምሁራን አቶ መለሰንና ግብረ-አበሮቻቸውን ለመምከርና ለማስተማር ያላደረጉት ጥረት አልነበረም። አቶ መለስም ሆነ ግብረ-አበሮቻቸው ህብረተሰብአዊ ባህርይ በመውሰድና ከህዝቡ ጋር የሚያቀራርባቸውን ስራ ከመስራት ይልቅ በተንኮል ላይ ተንኮል እየደረቡ አገርን በማዳከም ተግባራቸው ገፉበት። ከህዝብና ከምሁሩ የሚቀርባለቸውን ምክር ተቀብሎ ከማብሰልሰልና አብሮ ለመስራት ከመዘጋጀት ይልቅ ፣ ከኛ በላይ ማንም የሚያውቅ የለም በሚል አጉል ፈሊጥ ወደ ባሰ ወንጀል አመሩ። ከስህተት ሊማሩ የማይችሉና በድርጊታቸው ከእንስሳ

በታች የሆኑ ፍጡሮች መሆናቸውን እያረጋገጡ መጡ። እዚህ ላይ ነገሮችን ለያይቶ ማየት ቢቻልምና እያንዳንዱ ህብረተሰባዊ ፖለቲካ የየራሱ ሎጂክ ቢኖረውም በአጠቃላይ ሲታይ ስሌታቸውና ድርጊታቸው አገርን ከማዳከም ውጭና የራሰን የበላይነት ብቻ አስፍኖ ለዝንተ-ዓለም ለመፈንጨት ይቻላል ከሚለው አጉል ስሌት የመነጨ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። አቶ መለስና ግብረ-አበሮቻቸው በዚህ ድርጊታቸው ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው የሚሆን መኖሪያ ለማዘጋጀት አንድ ቦታ ቆም ብለው ማጤን እንደማይችሉ በአስራ-ዘጠኝ የግዛት ዘመናቸው አረጋግጠውልናል። በዓለም ታሪክ ውስጥ ብዙ በስልጣን የባለጉ አገዛዞች ቢኖሩም አንድን ህዝብ እንደዚህ በንቀት ያየና አገርን በግልጽ ያዳከመ ኃይል ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። ከኛዎቹ በስተቀር በቂም በቀልና በአወቅኹኝባይነት የተወጠረ አገዛዝ በዓለም ላይ እስከዛሬም አልተከሰተም።

ሰሞኑን በሰለሞን ተካልኝ በወጣው ዘፈን አቶ መለስን በዕውቀት እንደተካኑና ማንም እንደማይስተካከላቸው ተበስሮልናል። ብልሁና አዋቂው መሪያችን እንዲሁም አገርን መመምራት የሚችሉት እሳቸው ብቻ መሆናቸውን ተወድሶልናል። አቶ መለስና „ፓርቲያቸው“ ከስልጣን ቢወርዱ ያቺ ውድ አገራችን እንደምትፈራርስና አማራጭም ኃይል እንደሌለ ወይም ደግሞ መድረክ ምንም አማራጭ ፖለቲካ ማካሄድ እንደማይችል ይወራልናል። ስለ አቶ መለስ አዋቂነትና ብልህነት ሲወራልን ብዙ ነገሮች በአንድ ጊዜ ጭንቅላቴ ውስጥ መላወስ ጀመሩ። በመጀመሪያ ፕላቶ ይህንን በሰለሞን ተካልኝ የተዘፈነውንና በግብረ-አበሮቻቸው የሚወደሰውን ሙዚቃ ቢሰማ ኑሮ አስር ጊዜ መቃብሩ ውስጥ ይገላበጥ ነበር። ዕውቀት ሲባል ተራ ሽምደዳ ወይም የአካዳሚ ሙያነት አይደለም። አንድ ሰው አዋቂ ነው ሲባል አርቆ አሳቢም ነው ማለት ነው። ጭንቅላቱ በሞራልና በስነ-ምግባር የተገነባ ነው ማለት ነው። የመንፈስ ስላምንና ስርዓትን(Harmony and Order) ከጭንቅላቱ ጋር ያዋሃደ ነው ማለት ነው። ሃይማኖትን ከፍልስፍና ጋር አጣምረው ያስተምሩ የነበሩ ምሁራንም ሆነ የተፈጥሮንና የሰውን ልጅ ትርጉም ከንጹህ ፍልስፍና አንፃር ይመረምሩ የነበሩ ሊቃውንት ያስተምሩ የነበረው ፣ ትግሉ ሁሉ በዚህች ምድር ላይ የሰውን ልጅ ስቃይ መቀነስና የበለጠ ደስተኛ እንዲሆን ማድረግ እንደሆነ በጥብቅ ያሳስባሉ። ስለዚህ በፖለቲካ ዓለም ውስጥ የሚሳተፍ ለሰው ልጅ ጉዳት የማያስብና ፣ ጥሩ ነገር ለመስራት መዘጋጀት እንዳለበት የዕውቀት ዋናው አባት ፍልስፍና ያስተምረናል። አንድ አዋቂ መሪ በእኩልነት ላይ የሚያምንና በአንድ አገር ውስጥ እኩልነት ካልሰፈነ በስተቀር አልፎ አልፎ ህብረተሰብአዊ ትርምስ ሊመጣ እንደሚችል ስለዚህም ብልህነት የተሞላው ፖለቲካ ማካሄድ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የፍልስፍና ጠቢባን ያስገነዝቡናል። አዋቂ ሰው በጎሳ ፖለቲካ አያምንም። ፕላቶ አጥብቆ የጎሳ ፖለቲካን ይቃወም ነበር። በፕላቶን ፍልስፍና መሰረት የጎሳ ፖለቲካ ዘለዓለማዊ ብጥብጥን ስለሚያስከትል ፣ የፖለቲካ ሰዎች በተቻለ መጠን ፍቅርንና ወንድማማችነትን ማስተማር እንዳለባቸው ያስገነዝብ ነበር። አዋቂ ሰው በጥበብ የተካነ ነው። ሳይንስና ቴክኖሎጂን የሚያስቀድም ነው። አዋቂ ሰው በምንም መንገድ ቢሆን የብልግና ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ መንገዱን ሁሉ አያመቻችም። አዋቂ መሪ ለውብ ስራዎች ፣ ለጥበብና ለጥሩ ሙዚቃ ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። ከተማዎች በዕቅድና በስርዓት እንዲገነቡና ፣ አንድ ህዝብ ስርዓት ያለው ኑሮ እንዲኖር መመሪያ የሚሰጥና የሚያስተምር ነው። ከዚህ አጭር የፕላቶን ፍልስፍና መሰረት ስንነሳ የአቶ መለስ ድርጊትና የፖለቲካ ፍልስፍና በዕውነተኛ የዕውቀት ሚዛን ሊለካና እሳቸውንም እንደ አዋቂ ሊያሰኛቸው የሚያስችል አንዳችም ነገር የለም። በአዋቂው መሪያችን በአቶ መለስ የኢትየጵያ ህዝብ ፍዳዩን እንዲያይ ተደርጓል። የህሊናና የሰውነት ስቃይ ደርሶበታል። የአገራችን ነባራዊ ሁኔታና የህዝባችን ድህነት የሚያረጋግጡልን መሪዎቻችን በዕውነተኛው ዕውቀት ያልተካኑ መሆናቸውንና በቂም በቀል ተወጥረው በጥፋት ፖለቲካቸው እንደሚገፉበት ነው። ከዚህም በላይ አቶ መለስ በአስራ ዘጠኝ ዓመት የግዛት ዘመናቸው የኢትዮጵያ ህዝብ በምን ሁኔታ ውስጥ ይኖር እንደሆን ለማወቅ የተለያዩ የአገሪቱን ክፍለ-ሀገሮች እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ አልታየም። የከተማዎችና የመንደሮች ዕድገት ምን እንደሚመስሉ ፣ በየከተማዎችና መንደሮች ኢንዱስትሪዎች ይተከሉ አይተከሉ ፣ በገጠር ውስጥ የእርሻው ተግባር በስርዓት ይካሄድ አይካሄድ እየተዘዋወሩ አልጎበኙም። እንደ አንድ አገር መሪ የሚጠበቅባቸውን በፍጹም አላደረጉም። ታዲያ ምኑ ላይ ነው እንደ አገር መሪ የሚያሰቆጥራቸውና እንደዚህ ዐይነቱ ግጥም የሚገጠምላቸው። የኢትዮጵያን ህዝብ በመርገጣቸውና ዕድገቱን በማቀጨጫቸው እየተደሰቱ የሚኖሩ መሪ ይመስላሉ። ስለሆነም በአንዳች ነገር ከስልጣን እስከሚወገዱበት ጊዜ ድረስ በዚህ የጥፋት ስልታቸውና ድርጊታቸው እንደሚገፉበት ከአፋቸው ከምንሰማው ዛቻና ድርጊታቸው ማረጋገጥ እንችላለን። በዚህ ድርጊታቸው ምናልባት የታሪክን ሂደትና የህዝባችንን የስልጣኔ ጥማት ሊያራዝሙት ይችሉ ይሆናል። ከእንግዲህ ወዲያ ግን ኢትዮጵያን ሊበታትኗት በፍጹም አይችሉም። እነሱ ባልገመቱት ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁንም ለአገሩ ያለውን ፍቅር የባሰውኑ እያጠነከረ የመጣ ነው። ሊማሩ ያልቻሉትም ይህንን የህዝብ ውስጣዊ ስሜትና

ፍላጎት ጥበብ በተሞላበት ፖለቲካ ማካሄድ አለመቻል ነው። አስራ-ዘጠኝ ዓመት ከስህተቱ ያልተማረ አገዛዝ ከእንግዲህ ወዲያ ሊማር በፍጹም አይችልም።

## የወደፊቱ የትግል ስልታችን!

እስከዛሬ ድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ ያልሆነለት የተቃዋሚው ኃይል የፖለቲካ ስትራቴጂ ነው። የተቃዋሚው ኃይል የህዝባችንን ኃይል እንዴት እንደሚሰበስብና ትግሉን እንደሚያጠናክር የተሳነው ይመስላል። ትግሉን በአብዮታዊ ዲሞክራሲና በሊበራል ዲሞክራሲ ብቻ ውስጥ በማሽከርከር ለብሄራዊ ነጻነት የሚደረገውን ሰፊና የሰልጣኔ መሰረት እንዲዘነጋ ለማድረግ በቅቷል። ባለፉት አስራ-ዘጠኝ ዐመታት የፖለቲካ ተዋናይ ሆነው የወጡ ኃይሎች ዝናን ብቻ ከማትረፍ በስተቀር በሳይንስ በተፈተነና ዕውነተኛን ዲሞክራሲን ሊያቀዳጅ የሚችል ትምህርት ለህዝባችን ሲያስተምሩ አልታየም። በሆነው ባልሆነው የትግል ስልትና የርስ በርስ ሽኩቻ ህዝባችን መሪ አጥቶ ሞራሉ እንዲወድቅ ተደርጓል። ይህ ግን መብቃት ያለበት ይመስለኛል። ማንኛውም አገር በተወሰኑ መሰረተ-ሃሳቦች መገለጽና ህዝብም በነዚህ መሰረተ-ሃሳቦች ዙሪያ መሰብሰብ ያለበት ይመስለኛል። ለአንድ አገር ብሄራዊ-ነጻነት ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ ህብረተሰብና ቤተሰብ በተለያዩ ጭንቅላቶችን በሚያዳብሩ ዕውቀቶች መኮትኮት እንዳለባቸውና ግለሰብአዊ ነጻነትና ህብረተሰበአዊ ነጻነት አንድ ላይ የተሳሰሩና አንዱ ከአንደኛው ተነጥሎ ሊታይ እንደማይችል ግልጽ ሆኖ መቀመጥ አለበት። የመንግስትና የመንግስትን መኪና የሚቆጣጠሩ እነዚህን መሰረተ-ሃሳቦች የሚያስፋፉና የሚያዳብሩ ፣ እንዲሁም ደግሞ ህዝባዊ ኢንስቲቱሽኖችን ማቋቋም እንዳለባቸውና በመንግስትና በህዝብ መሀከል መደጋገፍ እንጂ መንግስት የህዝብ ጠላት ሳይሆን አለኝታ ፣ ህዝብ ደግሞ መንግስትን የሚቆጣጠርና ለአገር አንድነት ፀር የሆኑ ኃይሎች ሲነሱ እነሱን በመቃወም ውስጣዊ ጥንካሬ እንዲኖር በመተጋገዝ አገር እንዲገነባ የሚደረግበትን ሁኔታ መፍጠር ነው።

እስካሁን ድረስ በተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ እንደ ፈሊጥ የተወሰደውና ከደማቸው ጋር የተዋሃደው ትግል የምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያን ስልጣኔ እንደሚሻና በአውሮፓና በአሜሪካ ችሮታ ብቻ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕውነተኛውን ነጻነትና ብልጽግና ሊጎናጸፍ ይችላል ብሎ ማመንና ህዝብን በዚህ ዙሪያ ለማሰባሰብ መሞከር ነው። የታሪክን ማስረጃ ላገላበጠ የምዕራብ አውሮፓ መንግስታትና አሜሪካ አፍሪቃን በሚመለከት ግልጽ ዓላማ አላቸው። በእነሱ ዕምነት በአፍሪቃ ምድር ውስጥ በምንም ዐይነት ዕውነተኛ ስልጣኔ መምጣት የለበትም። የጥሬ ሀብቱ እየተዘረፈና ዕርዳታ የሚባል ነገር እየተለገሰለት የተዝረከረከ ኑሮ መኖር እንዳለበት የተደነገገ ነው። የምዕራብ አውሮፓና የአሜሪካ የፖለቲካ ፣ የሚሊታሪና የኢኮኖሚ ኤሊት በበላይነት የሚያምን ነው። እንደ አፍረቃ ያለው አህጉር ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛት አለበት። በነጻ ንግድ አማካይነት የሚደረገው ግፊት የበላይነትን ለመቀዳጀትና በአፍሪቃ ምድር ውስጥ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዳያብብ ለማድረግ ነው። ስለሆነም ወደ ውጭ ደካማ ፣ ወደ ውስጥ ደግሞ ጨቋኝ የሆኑ መንግስታትን ጠጋ በማለትና በመርዳት የስልጣኔው የጥማት ዘመን እንዲራዘም ማድረግ የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ተዋንያን ዋና ስትራቴጂ ነው። ይህንን ሀቅ መካድ ትልቅ የታሪክ ወንጀል እንደመስራት ይቆጠራል። ያለፈውን የስድሳ ዓመቱን የምዕራቡን ዓለም የውጭ ፖለቲካና ውስጣዊ ኃይል ያላገናዘበ ፖለቲካ ከአንድ ስህተት ውስጥ ወደ ሌላ በመክተት ለብሄራዊ ነጻነትና ለዕውነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚደረገውን ትግል እንዲዘናጋ ለማድረግ በቅቷል። ከዚህም ስንነሳ በአሜሪካንና በወያኔ መንግስት መሀከል ያለውን መተሳሰርና መደጋገፍ ነጥሎ ማየትና አገዛዙ የሚወስዳቸውን ፖሊሲዎች ሁሉ ከነሱ ቁጥጥር ውጭ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር የፖለቲካ የዋህነት ነው። በብዙዎቻችን የፖለቲካ ታጋይ ነን በምንል ዘንድ የተወሳሰበና ስትራቴጂያዊ (Complex and Strategic thinking) አስተሳሰብ ከሰውነታችን ጋር የተዋሃዱ አይመስልም። በአብዛኛው የተቃዋሚው ኃይል ዘንድ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና በተለይም በአሜሪካን ጉያ ስር መቆም መሀከል የተምታታ ፖለቲካ ሲካሄድ ይታያል። ማን ለምንና ለማን እንደሚታገል ግልጽ ካለመሆኑም የተነሳ አገራችንን የዘለዓለማዊ ጦር አውድማ ለማድረግና የፓኪስታንና የአፍጋኒስታን ዕጣ እንዲደርስባት አርቆ አሳቢነት የጎደለው ፖለቲካ ሲካሄድ ይታያል። በኛ ተቃዋሚ ነን በምንል ኃይሎች ዘንድ በግልጽና በመተማመን ውይይት ለማድረግ ፍላጎት ስለሌለ ሁሉም በየራሱ የትግል ስልትና ስሜት ብቻ እየተገፋ ለብሄራዊ ነጻነት የሚደረገው ትግል መልክ እንዳይኖረው እየተደረገ ነው። አንድ ሜዳ ላይ አስራ አንድ ኳስ ተጫዋቾች ግብ አግብተው አሸንፈው ከመውጣት ይልቅ ሁሉም በየፊናው በራሱ የጨዋታ ስልት እየተዝናና እየተደሰተ አብሮ ለሚጫወተው ኳስ ሳያቀብል ለመሮጥና ግብ ለማግባት እንደሚሞክረው ተጫዋጭ ሁሉ የኛም አገር የፖለቲካ ተዋናይ በየፊናው በመሽከርከር ለትግሉ እንቅፋት እየፈጠረ ነው። የፖለቲካ ትግል ፍልስፍናንና ዓላማን ይጠይቃል። መወያየትንና መመካከርን ይሻል። ግልጽነት ያስፈልገዋል። በአንድ አገርና

***ህብረተሰብ መሀከልና በውጭው ዓለም ጋር የሚኖረው የወደፊት ግኑኝነት ግልጽ ሆኖ መቀመጥ አለበት። አንድ ህዝብ ብቻ ራሱን ነጻ ሊያወጣ ይችላል ብሎ ግንዛቤ ሲገባና የዓለምን የተወሳሰበ ፖለቲካ በግልጽ ማስቀመጥ ሲቻልና ግንዛቤ ሲኖር ለስልጣኔ የሚደረገው ትግል የቀና ይሆናል። ከመዝረክረክና ከመራዘም ይልቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ድልን መቀዳጀትና በጋራ አገርን መገንባት ይቻላል።***

***በአጠቃላይ ሲታይ ሁሉም የተለያየ ስም ይዞ የሚታገል የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የብሄረ-ሰብ ነፃ አውጭ ነኝ ባይ ድርጅት ለተለያየች ኢትዮጵያ የሚታገሉ ነው የሚመስሉት። የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎትና ተግባራዊ እንዲደረግለት በሚፈልገውና አንዳንድ የተቃዋሚው ኃይል በሚመኘውና ተግባራዊ ለማድረግ በሚፈልገው መሀከል ትልቅ ልየኑት እንዳለ ይታያል። ዛሬ በግልጽ እንደሚታየው በብዙ አገሮች የፖለቲካ ኤሊቱ የመንፈስ ቀውስ ውስጥ ገብቷል። የየአገሩን ህዝብ ወደ አንድ ያልታወቀ ሁኔታ ውስጥ ለመክተት የሚጣደፍ የፖለቲካ ኤሊት ያለ ነው የሚመስለው። ይህም የሚያሳየው በዓለም አቀፍ ደረጃ የነጻ ገበያና የግሎባላይዜሽን ፕሮጀክት ፍጻሜው እንደተቃረበ ነው። ከሁለት ዓመት ጀምሮ በኢንዱስትሪ አገሮች የተከሰተው የፊናንስ ቀውስና ወደ ተጨባጩ የኢኮኖሚ ዘርፍ የተሸጋገረው ፣ ዛሬ ደግሞ በግልጽ የሚታየው የኦይሮ ቀውስ የነጻ ገበያ ፕሮጀክት ልቅ በሆነ መልክ ሊካሄድ እንደማይችል ነው ሁኔታው የሚያረጋግጠው። የየአገሮች በዕዳ መተብተብ ፣ መክፈል ያለመቻልና ዕጣቸው በጥቂት በፊናንስ በናጠጡ ከበርቴዎችና ኢንስቲቱሽኖች ውስጥ መውደቅ የሚያረጋግጠው የዓለም ማህበረሰብ ሌላ የስልጣኔ ፕሮጀክት እንደሚሻና እንደሚያስፈልገው ነው። ወደ አገራችንም ስንመጣ ከአስረሽ ምቺው ፖለቲካና የቁማርተኞች የነጻ ገበያ ፖሊሲ ባሻገር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ፖሊሲ ህዝባችንና አገራችን ከምንግዜውም በላይ እንደሚያስፈልጓቸው ሁኔታዎች በግልጽ ያረጋግጣሉ። ይጋብዛሉ። ወደ ውስጥ ሀብትን የሚያዳብር ፣ ለአካባቢ እንክብካቤ ቅድሚያ የሚሰጥ ፣ ዕደ-ጥበብን ከትናንሽና ከማዕከለኛ የኢንዱስትሪ ተከላ ጋር እያነጻጸሩ በመትከል በአገራችን ውስጥ የተስተካከለ ዕድገት ሊመጣ የሚችልበትን ሁኔታ የመንደፉ ጊዜ አሁን ነው። እያንዳንዱ አገር ከሌላው የሚማረው ነገር ቢኖረም አንድ ህዝብ የራሱ የሆነ ብሄራዊና ማህበረሰብአዊ ፕሮጀክት ያስፈልገዋል። አንድ ብሄራዊ ፕሮጀክት ደግሞ ሁሉም ኃይሎች ከሃይማኖትና ከብሄረ-ሰብ ልዩነት ባሻገር የሚነድፉትና የሚስማሙበት መሆን አለበት። ማንኛውም ሰው ለመኖር ሲል መብላት አለበት። የሚኖርበት አገር ያሰፈልገዋል። በዕቅድ የተሰሩ መንደሮችና ከተማዎች ያስፈልጉታል። ሃይማኖትና ጎሰኝነት ቅድሚያ ከተሰጣቸውና አንድም ህዝብ በዚህ ዐይነቱ ረዕዮተ-ዓለም ስር ከተሰበሰበ የስልጣኔው መንገድ ይጨልምበታል። ስለዚህም ማንኛውም ግለሰብ ቅድሚያ መስጠት ያለበት እንዴት አገሬን እገነባለሁ? ለተከታዩ ትውልድ የሚሆን መሰረት እንዴት እጥላለሁ ? ብሎ የሚታገል መሆን ያለበት እንጂ በአሳሳችና ተግባራዊ ወደማይሆን መፈክር በማድላት ህዝብን ወደ ማበጣበጥ ማምራት የለበትም። የአዋቂዎችና የአርቆ አሳቢዎች ህልም ህዝብን ለጋራ ዓላማ ማሰማራት ብቻ መሆን አለበት። ፍቅርን ማስተማር መሆን አለበት። ሰላም እንዲሰፍን ሳያቋርጡ መታገል መሆን አለበት። የትግላችን ዘዴና ዓላማ በነዚህ ዙሪያ ብቻ የሚሽከርከር መሆን አለበት። ይህ ከሆነ ለስልጣኔ የሚደረገው ትግል ቀና መስመር ይይዛል። አገራችንን ለማፈራረስም ሆነ የህዝባችንን ስቃይ ለማራዘም የሚታገሉትን ኃይሎች ዕድሜ ማሳጠር ይቻላል።***

**ፈቃዱ በቀለ**

**fekadubekele@gmx.de**